# የተሰውትንና በየጉድጓድ እስርቤቱ እየማቀቁ ያሉ ጀግኖቻችንን አንርሳ !! ቃል እናፍርስ!!

## ታምራት ግዛቸውና ጓዶቹ በወያኔ እጅ ከወደቁ 10 አመታቸው !!
## ሐምሌ 18 ቀን 1999ዓ.ም



ታምራት ግዛቸው በ1988ዓ/ም መጨረሻ ላይ የትጥቅ እንቅስቃሴ ጀምሮ የነበረው የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ጀማሪ የሽምቅ ጦር የፖለቲካ ሃላፊ የነበርና ሃምሌ 19 ቀን 1989 ዓ.ም በከሃዲ ጥቆማ ከሻለቃ አዱኛ አደመ ጋር በወያኔ እጅ የወደቀ የኢሕአፓ ነባርና ጠንካራ ታጋይ ነው። ታምራትና ሻለቃ አዱኛ አደመ በወያኔ እጅ ከወደቁ በኋላ መጀመሪያ ወደ መርትርድ ከዚያም ወደ ባህርዳር ከተወሰዱ በኋላ ደብዛቸው ጠፍቷል። በኢአግ እንቅሥቃሴ ወቅት መዳረሻቸው ከጠፋት ውስጥ ደግሞ መአዛ፤ ፈይሰል፤ ሃይለ ሚካኤል(ሁሉም የትግል ስሞች) ታደለ መንገሻና ድንቄ ሺፈራው ይገኙበታል።

ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች በመላ አገሪቱ በሚገኙ የጉድጓድ እስርቤቶች እየተሰቃዩ ነው። ታምራትና ሻለቃ አዱኛም ልክ እንደሌሎቹ በወያኔ እጅ እንደወደቁ የኢሕአፓ ታጋዮች እንደ ጸጋየ ገብረመድህን(ደብተራው)፤ ይስሃቅ፤ ሃጎስ በዛብህ፤ ተስፋየ ከበደ፤ ለማ ሃይሉ ፤ተክላይ ገ/ስላሴ፤ ደሳለኝ አምሳሉ፤ አበራሽ በርታ፤ እና ሌሎችም አያሌ ታጋዮች ሁሉ በነዚህ የጉድጓድ እስርቤቶች እየተሰቃዩ እንደሆነ ይገመታል።
በረጅሙ የትግል ጉዞ የተሰዉትና በወያኔ መዳፍ ስር ወድቀው እየማቀቁ ያሉ ታጋዮች ለቀረነው ታጋዮች የሰጡት አደራ ቢኖር ህዝብ የስልጣን ባለቤት እስኪሆን አብረን የጀመርነውን ትግል መቀጠልና ዳር ማድረስ ነው። የቀረነው ታጋዮች በአንዱ ወይም በሌላ ምክያት ቀበቷችንን ብናላላ ቃል እንዳፈርስን፤ እንደክህደትም ይቆጠራል።
በሌላ በኩል
ሉዓላዊነቷ የተጠበቀና የፍትህ የበላይነት ለነገሰባት ኢትዮጵያ የሚታገሉ ሃይሎች ሁሉ ብረት አንስተው ሆነ በሰላም ወያኔን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለማውረድ በተደረገውና እየተደረገ ባለው ትንቅንቅ ለተሰዉ ታጋዮች ክብር ሊሰጡ፤ በጉድጓድ እስር ቤቶች እየተሰቃዩ ያሉት ሁኔታ እንዲታወቅና እንዲፈቱ መጠየቅ መጀመር ይጠበቅባቸዋል።
ትግሉ የ1997 አይነት ህዝባዊ መነሳሳት ደረጃ ላይ ለመድረስና ኢትዮጵያም ወያኔና ሻቢያ እንደተመኙት ላለመፈረካከሷ ከሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ድርና ማግ የተሰሩ ታጋዮች ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ መሆኑን ማስተዋል ያሻል።
ስየ አብርሃምና ጓደኖቹም እነጸጋየ ደብተራውንና እነታምራትን woyane ምን እንዳደረጓቸው እንዲነግሩን ልንጠቃቸው ይገባል።

ትግሉ ይቀጥላል !

ከትግል ጓዶቻቸው
ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም.